# የአማራ መልሶ መቋቋምና ልማት ድርጅት (አመልድ)



## የዕለት ደራሽና የመልሶ መቋቋም ፕሮግራም ስራዎች

## 1977-1988 ዓ.ም

ባህርዳር

ታህሳስ 2001 ዓ.ም

# የበርካታ ሰዎች ህይወት ማዳን የቻለ እንቅስቃሴ

## 1. መግቢያ

የአማራ መልሶ መቋቋምና ልማት ድርጅት (አመልድ) ከተመሠረተ ከ25 ዓመት በፊት ጀምሮ በአማራ ክልል በድርቅና በጦርነት የተጎዳው ህዝብ ከችግሩ ለመላቀቅ የሚያደርገውን ጥረት በገንዘብ፣ በቁሳቁስና በቴክኒክ ለማገዝ የዕለት ደራሽ፣ የመልሶ መቋቋምና የልማት ፕሮጀክቶች በመቅረፅና በመተግበር እየተንቀሳቀሰ ያለ አገር-በቀል መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ነው፡፡ አመልድ በ1976 ዓ.ም ሲመሰረት እስከ 1987 ዓ.ም ይታወቅ የነበረው "የኢትዮጵያ ዕርዳታ ማስተባበሪያ ድርጅት (ኢዕማድ) ወይም በእንግሊዝኛ ''Ethiopian Relief Organization (ERO)" በሚል ስም ነበር፡ የዚህ ፅሁፍ ዓላማ አመልድ ከጅምሩ እንዴትና ለምን እንደተመሠረተና በተለይ ለአጠቃለይ ዕድገቱ መነሻ ሆነው ካገለገሉት የዕለት ደራሽና የመልሶ መቋቋም ስራዎች ዙሪያ ያከናወናቸው ዐበይት ተግባራትና ያስመዘገባቸው ውጤቶች ምን እንደነበሩ ጠቅለል አድረጎ ለማሳየት ነው፡፡ ይህን ፅሁፍ ለማዘጋጀት የሚረዱ መረጃዎች በማሰባሰብና በመፃፍ የቡድን አባላት ሆነው የተሳተፉት አቶ ዮናስ ገዳሙ፣ አቶ ደበበ በየነ፣ አቶ መንገሻ ጃቱ፣ አቶ ዘርፉ ፍቃዱ፣ አቶ አበራ አፍራሳና አቶ ይልማ መንግስቴ ናቸው።

## 2. አመልድ (ኢዕማድ) ለምንና እንዴት ተመሠረተ?

ወቅቱ በተለይ በ1976 እና 1977 ዓ.ም በርካታ የሰሜን ኢትዮጵያ አከባቢዎች በተደጋጋሚ ድርቅና ጦርነት የተጠቁበት ሁኔታ ነበር፡፡ በነዚህ ዓመታት በድርቅና በዝናብ እጥረት ምክንያት ምርት የጠፋበትና በተወሰኑ አከባቢዎች ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ የቀነሰበት ሁኔታ ነበር፡፡ እንስሳትም በሳር እጥረት ምክንያት በስፋት አልቀዋል፡፡ በሺዎች የሚቆጠሩ ወገኖች በረሀብ ምክንያት ቤት ንብረታቸውን እየጣሉ ሲሰደዱ ነበር፡፡ በተለይ በስልጣን ላይ የነበረውን የደርግን መንግስት ሲቃወም የነበረው የኢትዮጵያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢህዴን) ስር ሲተዳደር የነበረው የሰሜን ወሎና ጎንደር አከባቢ ህዝብ በአስከፊ ረሀብ፣ በሽታና ስደት ቢሰቃይም የደርግ መንግስት አከባቢዎቹ "አማፂያን" የሚንቀሳቀሱባቸውና የ"አማፂያን" ደጋፊዎች ናቸው በሚልና እርዳታን እንደ "ፖለቲካ መሣሪያ"

መጠቀም ከሚለው ፖሊሲው በመነሳት ከመንግስትም ይሁን ከአለም አቀፍ ለጋሾች ምንም ዓይነት እርዳታ እንዳያገኙ በመከልከሉ ህዝቡ በከፍተኛ ደረጃ የተጎዳበት ሁኔታ ነበር፡፡ ህዝቡ እርዳታ ፍለጋ ደርግ ወደሚቆጣጠራቸው የእርዳታ ጣቢያዎች በሚሄድበት ጊዜ ወንበዴዎችን ትደግፋላችሁ፣ ያሉበትን ካላሳያችሁ በማለት ደርግ እርዳታ ይከለክላቸውና ያንገላታቸው ነበር፡፡ በነዚህ ሁኔታዎች ምክንያት በርካታ ህዝብ በየመንደሩም ለስደት በሚጓዝበት በየመንገዱም የሚሞትበት ሁኔታ ነበር፡፡ ከድርቁ ጋር በተያያዘም በወረርሽኝ በሽታ ብዙ ህዝብ ተጠቅቷል ለሞትም ተዳርጓል፡፡

በተለይ በሰሜን ወሎና ጎንደር በድርቅና በጦርነት ምክንያት አደጋ ላይ የወደቀው ህዝብ ችግር ለመቅረፍ ሌላ የተዘጋጀ አካል ባለመኖሩ በወቅቱ በችግሩ የተቀጠቁትን አከባቢዎች ሲያስተዳድር የነበረው የኢትዮጵያ ህዝቦች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኢህዴን) ከአከባቢው ህዝብ ጋር በመነጋገር አንድ ሰብአዊ ድርጅት እንዲመሠረት ሀሳብ በማቅረቡና በፀጥታ ምቹ ሁኔታ በመፍጠሩ በየካቲት 1976 ዓ.ም በጎ ፈቃደኞች ተሰባስበው የ"ኢትዮጵያ ዕርዳታ ማስተባበሪያ ድርጅት (ኢዕማድ)" ወይም በእንግሊዝኛ "Ethiopian Relief Organization (ERO)" ለማቋቋም በቁ፡፡ ድርጅቱ እንደተመሰረተ ኢህዴን በሚያስተዳድራቸው አከባቢዎች በመቶ ሺዎች የሚቆጠር ህዝብ አደጋ ላይ ስለሆነ አስቸኳይ እርዳታ እንዲደረግለት የሚጠይቅ ፅሁፍ ለአለምአቀፍ ለጋሾች እንዲሰራጭ በማድረግ በውጪ እንቅስቃሴ አድርጓል፡፡ ከአለምአቀፍ ድርጅቶች ጋር ያለውን ግንኙነት ቀልጣፋ ለማድረግና ድጋፍ ለማሰባሰብ እንዲያመች ድርጅቱ በሱዳን ካርቱም በህግ ተመዝግቦ ፅ/ቤት ከፍቶ ተንቀሳቅሷል፡፡

ከ1977 ዓ.ም በኋላ እስከ 1983 ዓ.ም የደርግ ውድቀት ድረስም በቂ ዝናብ ባለመዝነቡ፣ አርሶአደሩ ተስማሚ የግብርና ቴክኖሎጂና ዘመናዊ የእርሻ ዘዴ ባለመጠቀሙ የምርት መቀነስና ቀላል የማይባል የምግብ እጥረት መከሰቱ አልቀረም፡፡ ከደርግ መንግስት ውድቀት በኋላም በተመሳሳይ ምክንያቶች በተለያየ ዓመታት በተለያየ ደረጃ ችግሩ በመቀጠሉ የምግብ ክፍተቱ ቀጥሏል፡፡ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት አመልድ (በፊት ኢዕማድ) በተከታታይ ዓመታት ያደረጋቸው እንቅስቃሴዎች ጠቅለል ባለመልኩ የሚከተሉት ነበሩ፡፡

## 2.2 የኢዕማድ መፍትሄዎች ምን ነበሩ?

### 2.2.1 የዕለት ደራሽ ፕሮግራም

ዓላማው በተከታታይ ድርቅና ጦርነት ምክንያት በረሀብና በሽታ የተጎዳውን ህዝብ በምግብና ቁሳቁስ በመርዳት ከሞትና ከመፈናቀል አደጋ መከላከል ያደረገ የዕለት ደራሽ ፕሮግራም በመቅረፅ ኢዕማድ ላደረገው የእርዳታ ጥሪ ለመጀመሪያ ጊዜ በ1977 ዓ.ም ምላሽ የሰጠው "የጀርመን ኤመርጀንሲ ዶክተርስ (GED)" የተባለ ግብረ-ሰናይ ድርጅት ነበር፡፡ በወቅቱ ኢህዴን የሚያስተዳድራቸው ለችግር የተጋለጡ አከባቢዎች የመኪና መንገድ ስላልነበራቸው የምግብ እህል (በዓይነት) በማጓጓዝ ህዝቡን መርዳት ስለማይቻል በቀጥታ የገንዘብ ድጋፍ እያገኘ የተሻለ አቅርቦት ካላቸው ገበያዎች እየሸመተ እንዲጠቀም ይደረግ ነበር፡፡

የፕሮግራሙ ትግበራ ከመጀመሩ በፊት በቅድሚያ መረዳት ያለባቸውን ተረጂዎች ለመለየትና ለመመዝገብ እንዲያመች በየአከባቢው የእርዳታና መልሶ መቋቋም ኮሚቴዎች እንዲቋቋሙ ይደረግ ነበር፡፡ ኮሚቴው ከጊአኮ (ጊዜያዊ አስተዳደር ኮሚቴ) ማለት በኢህዴን ነፃ መሬት የአስተዳደር አባላት ከነበሩ፣ ከኢዕማድ በጎ ፈቃደኛ ሰራተኞችና ከህ/ሰቡ የተውጣጣ ነበር፡፡ ተረጂዎች የሚለዩት የአከባቢው ህ/ሰብ በሚሳተፍበት ስብሰባ ነበር፡፡ በፀጥታ ምክንያት ስብሰባ ማድረግ በማይቻልበት ሁኔታ ህ/ሰቡ በሚስጢር ከኔ ይልቅ እሱ/እሷ ይረዳ/ትረዳ በሚል ምዝገባ ከጨርሱ በኋላ በይፋ በማይታወቅ ቀን ስርጭት ይካሄድ ነበር፡፡ በወቅቱ ህብረተሰቡ ተረጂዎችን ሲለይ እንደ ጥሩ ልምድ የሚወሰደው ከኔ ይልቅ እከሌ ይረዳ የሚል የመተሳሰብና የመተዛዘን ሁኔታ የነበረ በመሆኑ እርዳታው የተጎዱትን በማዳን ውጤታማ ነበር፡፡

በ1977 ዓ.ም ከተከሰተው ድርቅ ጋር በተያያዘ ከፍተኛ የኮሌራ በሽታ ወረረሽኝ ምክንያት በርካታ ሰዎች ይሞቱ ስለነበር በሽታውን ለመቆጣጠር መለስተኛ የህክምና አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ የህዝብ ሀኪሞች በማሰልጠን፣ ከጀርመን ኤመርጀንሲ ዶክተርስ በተሰጠ መድሀኒትና የህክምና ባለሙያዎች (አንዲት ዶክተርና ረዳት ሀኪም) ከፍተኛ ርብርብ በማድረግ በሽታው በቁጥጥር ስር እንዲውል ተደርገኋል። በተጨማሪ ነፃ የህክምና አገልግሎት ለመስጠት እንዲያመች

መሸሀ (ተከዜ ወንዝ) አንድ መለስተኛ ሆስፒታል በመክፈት ለህዝቡ ሰፊ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል።

ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ የደርግ መንግስት እስከወደቀበት 1983 ዓ.ም ድረስ ለተጎጂው ህዝብ ተከታታይ የዕለት ደራሽ ድጋፍ ተሰጥቷል፡፡ ድጋፍ ለማሰባሰብ የሚረዱ የዕለት ደራሽ ፕሮግራም ዕቅዶች ለማዘጋጀት በድርቁ የደረሰው የጉዳት መጠን የሚያሳዩ መረጃዎች በተለያየ አከባቢ ከሚገኙ የኢ.ዕማድና የጊዜያዊ አስተዳደር አካላት ይሰባሰቡ ነበር። ለአለምአቀፍ ለጋሾች የሚሰራጩ ወቅታዊ ዕሁፎችና መፅሄቶች ለማዘጋጀት የሚያግዙ መረጃዎች ከአገር ቤት ካርቱም (ሱዳን) ወደነበረው የድርጅቱ ፅ/ቤት በመገናኛ ሬድዮ ይተላለፍ ነበር። ኢ.ዕማድ ላቀረበው የአስቸኳይ እርዳታ ጥያቄ በቀዳሚነት ምላሽ ከሰጠው ከጀርመን ኤመርጀንሲ ዶክተርስ (GED) ብር 1,901,943.00 በ1977 ዓ.ም ተገኝቶ በገንዘብ መልክ በድርቁ ለተጎዱ 33,901 ሰዎች እንዲከፋፈል ተደርጓል፡፡ እርዳታው ሲሰጥ የነበረው በሁለት መልክ ነበር፡፡ ተጠቃሚዎች ብር እየተሰጣቸው የተሻለ ምርት ካላቸው አከባቢዎች በመሄድ እህል እንዲሸምቱና ከትርፍ አምራች አከባቢዎች በነጋዴዎች አመካኝነት እህል በመግዛት ለተጎጂዎች እንዲከፋፈል በማድረግ ነበር፡፡ እላይ እንደተጠቀሰው እርዳታው ለተጠቃሚዎች ሲሰራጭ የነበረው በዕለት ደራሽና መልሶ መቋቋም ኮሚቴዎች አስተባባሪነት ተረጂዎች በህ/ሰቡ ተሳትፎ ከተለዩ በኋላ ኢ.ዕማድ ባቋቋማቸው የስርጭት ኮሚቴዎች ነበር፡፡ በዚህ መንገድ ከ1977—1983 ዓ.ም በየዓመቱ ኢ.ዕማድ ባዘጋጃቸው የዕለት ደራሽ ፕሮግራሞች ጂኢ.ዲ፣ ኦክስፋም ዩኬ፣ ትሮኬር፣ ባንድ ኤይድ፣ ሬድ ባርና (ኖርወይ)፣ ክርስቲያን ኤይድና ካፎድ ከተባሉ አለምአቀፍ ግብረ ሠናይ ድርጅቶች በድምሩ ብር 16,092,936 በማሰባሰብ 893,175 ሰዎች እንዲረዱ ተደርጓል፡፡

የኢ.ዕማድ ሰራተኞች ህዝቡን ከሞትና ከስደት ለመታደግና ችግሩን ለማቃለል በቁረጠኝነት የተነሱ ስለነበር ሁሉም ያለ ደሞዝ በበጎ ፈቃደኝነት ይሰሩ ነበር። ኢ.ዕማድ መደበኛ በሆነ መንገድ ለሰራተኞች ደሞዝ መክፈል የጀመረው ከተመሰረተ ከ9 ዓመታት በኋላ በ1985 ዓ.ም ነበር፡፡ ሰራተኞቹ የከፈሉት መስዋእት ያለ ደሞዝ መስራታቸው ብቻ ሳይሆን ብዙ ውጣ ውረድ ባለበት፣ ህይወትን በሚያስከፍል በአስቸጋሪ የጦርነት ሁኔታ በመስራታቸውም ጭምር ነበር። እርዳታ

የሚሰራጭባቸው አከባቢዎች የመኪና መንገድ ያልነበራቸው በመሆኑና መኪናም ስላልነበር የድርጅቱ ሰራተኞች እርዳታ ሲያከፋፍሉ የነበሩት በእግራቸው እየተጓዙ፣ በሻንጣ ብር እየተሸከሙ ሲበዛም አህያና በቅሎ በመጠቀም ነበር። ለእርዳታ የሚውለው በሚሊዮዘኖች የሚቆጠር ብር ከዶላር ወደ ብር በውጪ ከተቀየረ በኋላ ወደ አገር ቤት የሚገባው ለቀናት በሚደረግ የእግር ጉዞና የደርግ መንግስት በሚቆጣጠራቸውና ሽፍቶች በሚንቀሳቀሱበቸው በሮችና መንገዶች በኢህዴን ሰራዊት ጥበቃ በሌሊት በመሻገር ነበር።

ከጊዜ ወደ ጊዜ የኢህዴን ነፃ መሬት እየሰፋና በውስጡ የሚኖረው ህዝብ እየጨመረ በመምጣቱ፣ በዛው ልክ በምግብ እጥረት ምክንያት ለአደጋ የተጋለጠው የህዝብ ቁጥርም እያደገ መጥቶ ነበር። ይኸን የተገነዘበው አለምአቀፍ ህ/ሰብ የደርግ መንግስት እርዳታን እንደፖለቲካ መሣሪያ አድርጎ መጠቀሙን ትቶ ሰብአዊ እርዳታ መንግስት ከሚቆጣጠራቸው "አማጺያን" ወደሚቆጣጠሩዋቸው አከባቢዎች ለማስተላለፍ ፈቃደኛ እንዲሆን ባደረጉት ተፅዕኖ መሰረት ስምምነት ተደርጎ የዕለት ደራሽ ድጋፍን በአጋርነት ለመስጠት በተሰባሰቡ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች (JRP) እንዲጓጓዝ ተደርጎ ህዝቡ የሚረዳበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር። በዚህ ስምምነት መሰረት የእርዳታ ስርጭት ማዕከላት ተብለው ከሚታወቁት ዙሪያውን እስከ 500 ሜትር ርቀት ድረስ የአውሮፕላን ድብደባን ጨምሮ ምንም ዓይነት ጦርነት እንዳይካሄድ የተከለከለ ነበር። ነገር ግን የደርግ መንግስት ስምምነቱን በመጣስ ታህሳስ 1983 ዓ.ም የወልዲያ ከተማን በአውሮፕላን በመደብደብ ከእርዳታ መጋዘን ፊት ለፊት የነበረውን የኢዕማድ ፅ/ቤትንና የህዝብ መሰብሰቢያ አዳራሽ ሙሉ በሙሉ አውድሟል። ለስራ ማስኬጃና ለፕሮግራም ተረጂዎች የተመደበ ከመቶ ሺ በላይ የሚገመት ብር፣ ሰነዶችና የተለያዩ ንብረቶች ተቃጥሏል። የጄይአርፒ (JRP) እርዳታ ሰጪዎች ሲጠቀሙበት የነበረው መጋዘንም በከፊል ፈርሷል። በአውሮፕላን ድብደባው ምክንያት ህፃናትና ሴቶችን ጨምሮ በርካታ የከተማው ነዋሪዎች ሙትና ቁስለኛ ሆነዋል። በወቅቱ በኢዕማድ ጽ/ቤት ከነበሩት ሰራተኞች መካከል የተወሰኑት ቆስለዋል። እዚህ ላይ በተለየ በአርአያነቱ መነሳት የሚገባው ጉዳይ የጦር አውሮፕላኖች (2 ሚግ፣ 2 ሄሊኮፕተሮችና አንድ ሰሲና የቅኝት አውሮፕላን) ከተማዋን ሲዞሩና በርካታ ሰው ቦታ ለመያዝ ሲሯሯጥ የድርጅቱ መኪናና ንብረት

በአውሮፕላን እንዳይመታ ለራሳቸው ህይወት ሳይሳሱ በቆራጥነት ሽራ እያለበሱ በማመሳሰል ላይ እያሉ ተመትተው ስለቆሰሉ ሁለት የኢዕማድ ሰራተኞች ነው። ከሁለቱ አንደኛው በበግራ ክንዱ ከባድ ስብራት የደረሰበት በወቅቱ የኢዕማድ የኢንፎርመሽንና የማስተዋወቅ ክፍል ሀላፊ የነበረው አቶ ደበበ በየነ ሲሆን ሁለተኛው ወገቡ ላይ የተመታው በወቅቱ የኢዕማድ ምክትል ሀላፊ የነበረው አቶ ሀይሉ ፈንቴ ነበር።

ኢዕማድ በ1977 ዓም እና በቀጣዮቹ ዓመታት በአስቸጋሪ የጦርነት ሁኔታ እርዳታውን እንዴት ሲያሰራጭ እንደነበር በወቅቱ የኢዕማድ ስራ አስፈፃሚ አባልና የዕለት ደራሽ ስራዎች ሲያስተባብሩ የነበሩት አቶ ልጅአለም ወልዴ (በአሁኑ ጊዜ የዋግ ኽምራ ዞን ም/ቤት አፈ ጉባኤ) ሁኔታውን እንዲህ ይገልፁታል፡፡



አቶ ልጅአለም ወልዴ (የኢዕማድ ስራ አስፈፃሚ የነበሩ መሀል ላይ የተቀመጡት)

“የኢትዮጵያ እርዳታ ማስተባበሪያ ድርጅት /ኢእማድ/ /ERO/ ሲመሠረት በዋግኽምራ አከባቢ ከፍተኛ ድርቅ ነበር፡፡ በዚያን ወቅት ዋግ የትጥቅ ትግል የሚካሄድበት አከባቢ ስለነበር በወቅቱ የነበረው የደርግ መንግሥት የዋግ ሕዝብ ከተለያየ እርዳታና ጥቅም እንዲገለል አድርጎት ነበር፡፡ እርዳታን እንደ ፖለቲካ መሣሪያ አድርጐ ይጠቀምበት ነበር፡፡ ለምሣሌ ደርግ ኢህዴንን አስለቅቆ የሰቆጣ ከተማን በተቆጣጠረበት ወቅት በጊዜው ዕርዳታ ቢያቀርብም ለዕርዳታ የሚመጣውን ሕዝብ ‘እናንተ የገንጣይ አስገንጣይ ደጋፊ ናችሁ፣ ያሉበትን ቦታ ካላሳያችሁ፣

ወንበዴዎችን እያበላችሁ እያጠጣችሁ" በሚል ዕርዳታ አንሰጣችሁም ይላቸው ነበር፤ በዱላ በመደብደብና በማሰር ከፍተኛ በደል ያደርስባቸው ነበር፡፡ ከዕርዳታ ለማግለል ቅድም እንዳልኩት ዕርዳታን እንደፖለቲካ መሣሪያ ተጠቅሞበታል፡፡ በዚህ ምክንያት ህዝቡ ከደርግ ዕርዳታ ከመቀበል ይልቅ ወደ ሱዳን መሰደድ ይሻላል ይል ነበር፡፡ በወቅቱ ኢህዴን የውጭ ክንፍ ስለበረው ህዝቡ ዕርዳታ የሚያገኝበትን ሁኔታ በማጥናት አንድ ማህበር እንዲመሠረት ሀሳብ አቅርቦ በአገር ውስጥ የነበርነው የተወሰኑ ሰዎች ጉዳዩን ተቀብለን የእርዳታ ድርጅት ተመሠረተ፡፡ በወቅቱ ዕርዳታ ሲመጣ የነበረው በገንዘብ መልክ ከውጪ ሲሆን በዓይነት ማስገባት አይቻልም ነበር፡፡ ምክንያቱም መንገዶች ሁሉ ዝግ ነበሩ፡፡ በተጨማሪ የመድሃኒት ድጋፍ ይደረግ ነበር፡፡ በወቅቱ እኔ እንደማስታውሰው እጅግ በጣም ዘግናኝ ረሃብና የኮሌራ በሽታ ስለነበር ህዝቡ እህል ፍለጋ ሰሜን ጐንደርና ወልቃይት አካባቢዎች እየተሰደደ በመንገድ ላይ የሰውና እንስሳት እሬሳ ተደባልቆ ነበር የሚገኘው በርካታ ሕይወት ነው ያለቀው፤ በወቅቱ የተከሰተውን የኮሌራ በበሽታ ለመቋቋም ኢህዴን በርካታ ህዝባዊ ሃኪሞችን በማሰልጠን አሰማርቷል፤ ህዝባዊ ሀኪሞች በማይደርሱበት አካባቢዎች የሠራዊቱ ሃኪሞች የህክምና አገልግሎት ሠጥተዋል፡፡ በዚህም የበርካታ ሠዎች ህይወት ማትረፍ ተችሏል፡፡

በአጠቃላይ ወቅቱ በጣም ዘግናኝ ነበር፤ እንስሳት አይሸጡም፣ አይለወጡም መንገዱ ሁሉ እንስሳት ወድቀው የሚታዩበት ነበር፡፡ ውሃ ስላልነበረ ብዙ ሠው ውሃ እያለ መንገድ ላይ የሚቀርበት ሁኔታ ነበር፡፡ እንደዚሁም በወቅቱ ድርጅቱን የሚመራ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ነበር፡፡ እነሱም አቶ ዮናስ ገዳሙ፣ አቶ ልጅለም ወልዴ፣ አቶ አለማየሁ ደንፉ፣ እና አቶ አድማሱ ጋጋ ሲሆኑ የሚመራቸውም አቶ ሀይሌ ጥላሁን ነበር፡፡ እነዚህ ከላይ ሥራውን ያስተባብሩ ነበር፡፡ በተለይ እኔ እና አቶ አድማሱ ጋጋ አቶ አለማየሁ ደንፉ የእለት ደራሹን ሥራ ስናስተባበር ነበር፡፡ ወደ ደሃና፣ በለሳና ዝቋላ ገንዘብ በሻንጣና በአጋሰስ በመጫንና በሠራዊት ታጅበን እንሄድ ነበር፡፡ በእደላ ወቅት ብዙ አስከፊ ሁኔታዎች ይገጥሙን ነበር፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ለዕደላ ምዝገባ ሲካሄድና ዕደላ ስንጀምር የጠላት ሽምቅ መጥቶ ዕደላውንና ምዝገባውን ያደናቅፍብን ነበር፣ በውጊያ መሀልም ለህዝቡ እርዳታ ይሰጥ ነበር ፣ እደላው እንዳይደናቀፍ የፀጥታን እንቅስቃሴ እየተከታተለ መረጃ ሲሰጠን የነበረው

ሕዝቡ ነው፡፡ የጠላት የማደናቀፍ ሙከራ ለመቋቋም ማታ በጨለማ ተረጂዎችን እየመዘገብን የማደል ስራ እናከናውን ነበር፡፡ በወቅቱ የስርጭት መመሪያ መሰረት ለአንድ ሰው ለአንድ ወር ሊሆን የሚችል በ15 ኪ/ግራም እህል ሒሳብ በብር ይሰጥ ነበር፡፡ እንደዚሁም እንደገበያው ሁኔታ ከ15-20 /ብር/ ይሰጥ ነበር፡፡ ህዝቡ የዕለት እርዳታ እያገኘና እራሱን እየመራ ሳይሰደድና በሙሉ ቤቶች ሳይዘጉ በአካባቢው እንዲቆይ ተደርጓል፡፡ ኢሮ/ERO/ ለዋግና ለበለሳ ህዝብ በጣም ባለውለታ ነው፡፡ በጣም ከማስታውሰው አንዱ በዕደላ ወቅት በመታማቸው ምክንያት መምጣት ላልቻሉ እስከ ቤታቸው ድረስ እየሄድን እንሰጥ ነበር፡፡ በተጨማሪ ሀኪሞችም ቤት ለቤት በመሄድ ህክምና ይሰጡ ነበር፡፡ የተሠራውም ሥራ የፖለቲካ ሥራ ሳይሆን በጣም ሰብአዊነት ያለው ሥራ ነው የተሠራው፡፡ በቅርቡ ዝቋላ /ፅፅቃ/ ሄጀ አንድ ስሙን ላስታውሰው ያልቻልኩት ልጅ አባቱ የነገረውን ሲነግረኝ “እኔ በኢሮ /ERO/ ድጋፍ ከሞት የዳንኩ ነኝ ኢሮ የሚባሉት እኔ ልጅአለም መጥተው አክመውኝ የተረፍኩ ነኝ” ብሎኛል ብሎ የነገረኝን ትዝ ይለኛል። በወቅቱ ቤት ለቤት ነበር ህክምናም እርዳታም የሚሰጠው፡፡ ከእኛ ጋር በወቅቱ ሞገስ አሰፋ የሚባል ሐኪም ነበር አብሮ ህክምና ሲሰጥ ነበር፡፡ የብዙ ሰው ሕይወት እንዲተርፍና መንደሮች ባድማ ከመሆን እንዲተርፉ ሆነዋል፡፡ በወቅቱ ብዙ ሰው በኮሌራ በሽታ ስለተያዘ ኦአርኤስ /ORS/ የሚባል መድሃኒት በስፋት ይታደል ነበር፡፡ ህዝቡም በሽታን እንዴት መከላከል እንዳለበት የግንዛቤ ትምህርት በስፋት ይሰጥ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከውጭ በኢሮ /ERO/ በኩል በተገኘ ዕርዳታ መለስተኛ ሆሰፒታል ተከዜ ውስጥ ተቋቁሞ ነበር፡፡ ሕዝባዊ ሃኪሞች ሪፈር የሚሏቸው ከየገጠሩና ከየበረሃው በበሽታ የተጠቁ ሰዎች ወደ ሆስፒታሉ እየመጡ ይታከሙ ነበር፡፡ በወቅቱ በሆስፒታሉ የጀርመን ሃኪሞች ይገኙ ነበር፡፡ በተጨማሪ የሰለጠኑ ህዝባዊ ሃኪሞችና የሠራዊቱ ሃኪሞች ለሕዝቡ የህክምና አገልግሎት ይሰጡ ነበር፡፡ ይህ ሲደረግ በአካባቢው የህክምና ስራው እንደይደናቀፍ የኢህዴን ሠራዊት የደርግን እንቅስቃሴ በአስተማማኝ ሁኔታ መግታት የቻለበት ሁኔታ ነበር፡፡ ከጊዜ በኋላ የኢህዴን ነፃ መሬት እየሰፋ ሲሄድ እርዳታው ከብር ወደ የአይነት ዕደላ የተሸጋገረበት ሁኔታ መጣ ይህን ለማድረግ ነጋዴዎች እህል ገዝተው በመጠነኛ ትርፍ እንዲያቀርቡ ይደረግ ነበር፡፡ በዚህ እንቅስቃሴ ሁለት ጠቀሜታዎች ነበሩ፤ በአንድ በኩል ነጋዴዎች ሲጠቀሙ በሌላ በኩል ተረጅው ህዝብ በብር ከገበያ እህል ስለማያገኝ

ነጋዴዎች ከሌላ አካባቢ አፈላልገው ህዝቡ የእህል እርዳታ እንደያገኝ የተደረገበት ሁኔታ ተፈጠረ፡፡ ቀስ በቀስ ህዝቡ ከእርዳታ እንዲላቀቅ በኢ.ሮ /ERO/ ገበሬዎች የበሬ፣ የእርሻ መሣሪያ፣ ዘር እየተሰጣቸው እራሳቸውን እንዲችሉ የመልሶ መቋቋም ኘሮግራም እንዲጀምር ተደርጓል" ብለዋል፡፡

አቶ ሰለሞን በሰቆጣ ወረዳ አስተዳደር ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባል ከአመልድ እንደ ጥሩ ተሞክሮ ነው ብለው የሚያስተውሱት "በእርዳታ ማስተባበርና ማሰራጨት ሲሰሩ የነበሩ የስርጭት ቡድኖች በእቅዱ መሰረት ለህዝቡ መቅረብ ያለበት ድጋፍ (ገንዘብ) ምንም ህይነት ማጭበርበር በሌለበት መንገድ ለህዝቡ በማድረስ ግዴታቸውን ይወጡ ነበር፡፡ በህ/ሰቡ በኩልም መረዳት ያለባቸው ሰዎች በትክክል በህዝቡ እየታመነባቸው ከኔ ይልቅ እከሌ ይረዳ በሚል ከማጭበርበር ነፃ በሆነ መንገድ እርዳታው እንዲሰጥ ያደርጉ ነበር"፡፡

አቶ ልጅ አለም ወልዴ በእርዳታ ስርጭት ላይ ያጋጠማቸው ገጠመኞች በበኩላቸው ሲገልፁ "እኔም እንደማስታወሰው ኢህዴን ውስጥ የነበረው አስተሳሰብ ህዝቡ ውስጥ ሰርፆ ስለነበር ከእኔ ይልቅ እሱ ይረዳ የሚል አስተሳሰብ በህዝቡ ውስጥ ሰፍኖ ነበር፡፡ ይኸ ጥሩ ነገር ነበር የማጭበርበር ስራ ይኖራል ተብሎ አይጠረጠርም፡፡ ድርጅቱ ውስጥ እውነተኛ ያልሆነ ሰው በጣም ይወቀሳል፡፡ እውነተኛ የሆነ ሰው ደግሞ በጣም ይበረታታል፡፡ ጥፋት እንኳ አጥፍቶ እውነቱን ከተናገረ በጣም ነበር የሚበረታታው እንዳሁኑ ፍርድ ቤት እውነት ከተናገርክ እስር ቤት ትገባለህ፡፡ ከዋሸህ ወይም ሀሰት ከተናገርክ ትወጣለህ በሚል አይሄድም፡፡ በመረጃ ሳይሆን በህሊናው እራሱ ምስክር በሌለበት በራሱ ግለሂስ እያደረገ ይሄድ ነበር፡፡ ይኸ ህዝቡ ውስጥ ነበር፡፡ ህዝቡ እራሱ ተሰባስቦ ጥፋት ያጠፋ ካለ እራሱ ጥፋቱን እንዲያምን ያደርግ ነበር፡፡ ይኸ አስተሳሰብ የተሻለ የበላይነት ስለበረው በህዝቡ ውስጥ መተማመን ነበር፡፡ መሪው ውስጥ እንዲህ ዓይነት አስተሳሰብ መኖር አለበት ከመሪው ወደ ህዝብም መተላለፍ አለበት፡፡ እንዲህ ዓይነት የእርዳታ ስራ ሲሰራ በትንሽ ሰው ነበር ምዝገባ የሚካሄደው ስርጭትም የሚደረገው። ብር አቅፈህ ትሄዳለህ ብሩ ቅጠል ነው ድንጋይ ነው ለአንተ አይታይህም በጣም ይናቃል የዚያን ጊዜ፡፡ ሌላም እኔ እንደ ልዩ ገጠመኝ የማነሳው የዕለት ደራሽ በመስራት ላይ እያለን ጀርባ የሚባል ቦታ ላይ ያጋጠመንን ነው፡፡ ከሰዓት ገብተን ማታ ነበር ማደል

የጀምርነው እያደልን እያለን መሸ ምን እንደምናድል አያታይም ነበር፡፡ ጨለመብንና ተመልሰን የኢህዴን ሰራዊት ባለበት ተኛን፡፡ ብር የያዘ ሻንጣ ስለያዝኩ ጠላት ይመጣል ብዬ ሳልተኛ ስገላበጥ ነበር ያደርኩት፡፡ እየነጋ ነው ብዬ የተኛኹት ወደ አስር ተኩል ነበር፡፡ ከተኛሁበት አንድ ጥበቃ ብር የያዘውን ሻንጣ ይዞ ከሄደ በኋላ ለእርዳታ የሚመጣው ሰው ጥዋት ስለመጣ አንዱ ከስርጭት ቡድኑ "አንተ፣ ሰው መጥቷል ተነስ" ሲል ስነሳ ሻንጣው የለም፡፡ አንተ ይኽን ሻንጣ የት ወሰዳችሁት መልሱት እላለሁ ቀልድ  መስሎኝ ይሰረቃል ብዬ ስላላሰብኩ፣ እረ የለም ምን ትቀልዳለህ ይሉና እንሳሳቃለን፡፡ በኋላ የለም ሰው ቁጠሩ ሲባል የመጨረሻ ዋርድያ (ጥበቃ) የለም ተባለ ተፈለገ ጠፋ እስከ ሰቆጣ ድረስ ደርግ ስለነበር ሰቆጣ ይገባል ተብሎ ተፈለገ ሰውየው የቡግና ልጅ ነው፡፡ ወደ ትግሉ በቅርብ ጊዜ የተቀላቀለ ነበር፣ ብሄራዊ ውትድርና አልሄድም በሚል የመጣ ነበር፡፡ የተማርኩ ነኝ የሚል መምህር ነበር፡፡ ሻንጣው ውስጥ የነበረውን ወረቀትና ሰነድ ቀዳዶ አንዱ በረሃ ላይ መጣሉን ምልክት ተገኘ የጦር መሳሪያ ይዞ ስለነበር እያጭበረበረ ሰራዊቱ በየት በኩል ሄደ እያለ አለፈ፣ ወደ ደርግ ገባ፡፡ ሁላችንም በብስጭት በሽተኛ ሆን ስራዊቱ ወባ ያዘው፣ ደነገጠ፣ ህዝቡም አለቀሰ፣ ብሩ ጠፋ። በድንጋጤ አንድ አርሶአደር ሞቷል የሚተማምንባት እስዋ ስለነበረች፡፡ መጨረሻ ሲባል ሲባል አገር ተያዘ (ደርግ ወደቀ)። እኛ ጋር የነበሩ ሰራዊቶች አዲስ አበባ ሲገቡ አገኙት። አዲስአበባ ጨረቃ ቤት ሰርቶ ነው የተያዘው። እኔ ደሴ እያለሁ ነበር መልዕክት ደርሶኝ የሰማሁት። እኔ በዚሁ ምክንያት በውስጤ በተፈጠረው ውጥረት ፈተና ደርሶብኛል፡፡ ሁሌ አስታውሰው ነበር፡፡ መቼ ነው ይኽን ሰው የምናገኘው እንል ነበር ለእኔና ለኢህዴን ታጋዮችም መጥፎ ገጠመኝ ስለነበር ሁሌ እናስታውሰው ነበር፡፡ ሰው ሁሉ አልቅሷል፡፡ ወባ ያለብን ሰዎች ሁሉ ወባ ተነሳብን። የተያዘው ግለሰብ ከአዲስአበባ ወደ ደሴ መጣ። የጠፋው ከጀርባ ስለነበር ለጀርባ ህዝብ አቀረብነው፡፡ ህዝቡን ሰብስበን ያንተን ብር  የወሰደው ከአዲስአበባ ተይዞ መጥቶልሀል ስንለው የጀርባ ሕዝብ እንባ በእንባ ሆነ፡፡ ህዝቡ ቁጭ ብሎ ተነጋግሮ ውሳኔ ሰጠ፡፡ የሞት ፍርድ የሚልና 10 ዓመት ይታሰር በሚል ክርክር ከተካሄደ በኋላ በጥቂት ድምፅ እስራት የሚለው ስለበለጠ እንዲታሰር ሆነ። ፍ/ቤቱ መጨረሻ የወሰነው ምን ላይ እንደደረሰ ግን አልታወቀም" ብለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የእርዳታ ስርጭት በሚካሄድበት ወቅት ስራውን ለማደናቀፍ የደርግ ጦር

የሞከረው ድርጊት በሚመለከት አቶ ልጅአለም ያጋጠማቸውን ሁኔታ እንደሚከተለው ይገልፁታል። "አመልድ (ERO) እንዲመሰረት ትልቁን ሚና የተጫወተው ኢህዴን ነበር፡፡ ኢህዴን ህዝባዊ ወገንተኝነቱን ካረጋገጠበት መንገዶች አንዱ ነው፡፡ ኢህዴን በሚያስተዳድረው አካባቢ ወይም በኢህዴን ነፃ መሬት የሚኖር ህዝብ ችግር ለመፍታት ውጪ ከነበሩ አካላት ኢዕማድ እንዲመሰረት ምቹ ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ በኢህዴን ነፃ መሬት ያለው ህዝብ ከድርጅቱ ጋር በመወገኑ ደርግ ህዝቡን እርዳታ በመከልከል የተበቀለበት ሁኔታ ነበር። ይኸን ችግር ለመፍታት ኢህዴን ባለው ውሱን አቅም ብዙ መስዋእት ከፍሏል፡፡ በውጪ ኢዕማድ ተቀባይነትና እርዳታ እንዲያኝ ብዙ ጥረት ተደርጓል፡፡ ጠላትን ከውጪ ከመከላከሉ ሌላ በውስጥም ሌት ተቀን የጠላት እንቅስቃሴን በመከላከል የእርዳታ ስራ እንዳይደናቀፍ አድርጓል፡፡ ለምሳሌ ቀውዝባ ከተማና ጥላላ (ደሀና ወረዳ) አካባቢ አንዲት የድርጅቱ ቡድን የእርዳታ ስርጭት በምታካሂድበት ጊዜ ጠላት ሰምቶ አንድ ሻምበል ጦር አንቀሳቅሶ እደላውን ለማደናቀፍና ገንዘቡን ለመንጠቅ ሲሞክር የኢህዴን ሰራዊት ከደርግ ጦር ጋር በመዋጋትና መስዋዕት በመክፈል ስርጭቱ ሳይቋረጥ ገንዘቡም ሳይነጠቅ ስራው እንዲከናወን አድርጓል፡፡ ሌላ በእርዳታ እንቅስቃሴ በርካታ ፈተናዎች ነበሩ፡፡ ከነዚህ መካከል የማስታውሰው የኢዕማድ ስራዎች ሲያስተባብር የነበረው አለማየሁ ደንፉ በለሳ ስራ ላይ ቆይቶ ተከዜን ሲሻገር በጎርፍ ተወስዶ መስዋእት የሆነበት ሁኔታ ነበር" ብለዋል፡፡

ከመንግስት ለውጥ በኋላ አመልድ ከ1984-2001 ዓ.ም ድረስ በድምሩ በአማራ ክልል ደረጃ 1,923,998 ቶን ምግብ በየዓመቱ በአማካይ ለ1,621,152 ተጠቃሚዎች አከፋፍሏል። እላይ ከተጠቀሰው የምግብ ድጋፍ አብዛኛው ወይም 1,679,735 ሜ/ቶን የተገኘው በአማራ ክልል የምግብ ዋስትና ማስተባባሪያና አደጋ መከላከል ፅ/ቤት (በፊት አመዝኮ) በኩል ሲሆን ቀሪው 243,860 ሜ/ቶን ወይም 12.7 % አመልድ ከተለያዩ ለጋሾች ያሰባሰበው ነው። በአጠቃላይ አመልድ ከምስረታው ጀምሮ በ25 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ለዕለት ደራሽ ፕሮግራሙ ብቻ ከተለያዩ ለጋሾች ብር 105,603,311 እና 1,923,998 ሜ/ቶን ምግብ በየዓመቱ በአማካይ ለ1,221,571 ተጠቃሚዎች እንዲከፋፈል አድርጓል።

### 2.2.2 የግብርና መልሶ መቋቋም ፕሮግራም

ኢ.ዕማድ የረሀብ ችግር በአጭር ጊዜ የዕለት ደራሽ ፕሮግራም ይቀረፋል ብሎ ስላላመነ በድርቁ ምክንያት የጠፋውን የአርሶ አደሩን የማምረት አቅም እንደገና በመገንባት እራሱን የሚችልበት ሁኔታ እንዲፈጠር "የግብርና መልሶ ማቋቋም ፕሮግራም" በመቅረፅና ከተለያዩ ለጋሾች የፋይናንስ ድጋፍ በማሰባሰብ የእርሻ መሬት ላላቸው ገበሬዎች በሬ፣ የእርሻ መሣሪያዎችና ዘር በመስጠት ድጋፍ አድርጓል፡፡

#### 2.2.2.1 የግብርና መልሶ ማቋቋም ፕሮግራም አስፈላጊነት

በ1977 ዓ.ምና በቀጣዮቹ ዓመታት ተደጋጋሚ የድርቅ ሁኔታዎች የነበሩ በመሆኑና ለነዚህም የአርሶአደሩ ጥሪት ወይም ሀብት እንዳይሟጠጥ የሚከላከል ወቅቱን የጠበቀ ምላሽ በነበረው የደርግ መንግስት ባለመሰጠቱ፣ አርሶ አደሩ በሬዎቹ፣ ዘሩና ንብረቱን አጥቶ የሚሰደድበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡ በርካታ አርሶ አደሮች ዝናብ ቢዘንብም ከድርቁ በፊት የዓመት ምግባቸውን አምርተው እራሳቸውን መመገብ ወደሚችሉበት ደረጃ መድረስ የሚችሉበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ ችግሩን ለመቅረፍና ተጎጂዎች ከተደጋጋሚ ተረጂነት እንዲላቀቁ ለማድረግ የገበሬዎች የማምረት አቅም መልሶ መገንባት አስፈላጊ ነበር፡፡ ይህንን ምክንያት በማድረግ ነበር የግብርና መልሶ መቋቋም ፕሮግራም እንዲዘጋጅ የተደረገው፡፡

#### 2.2.2.2 ወደ ልማት ያሸጋገረ የመልሶ መቋቋም ፕሮግራም

በግብርና መልሶ መቋቋም ፕሮግራም በሺዎች የሚቆጠሩ አርሶአደሮችን ለማቋቋም ለተለያዩ ለጋሾች ኢ.ዕማድ (አመልድ) ባቀረበው ጥያቄ መሠረት ከ1978 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1983 ዓ.ም ድረስ ብር 2,938,948.00 በማሰባሰብ ለ7,116 ገበሬዎች (የቤተሰብ ሀላፊዎች) የበሬ፣ የእርሻ መሣሪያዎችና የዘር ድጋፍ ተደርጓል፡፡ ለዚህ ፕሮግራም ድጋፍ የተገኘው ከትሮኬር፣ ከኦክስፋም ዩኬና በኦክስፋም ዩኬ ከሚመራው የመንግስታዊ ያልሆኑ አለምአቀፍ ድርጅቶች ስብስብ (ባንድ ኤይድ፣ ኦክስፋም ዩኬ፣ ክርስቲያን ኤይድ ከመሳሰሉት) ነበር፡፡ በፕሮግራሙ መሠረት አርሶአደሮች የበሬና የሌሎች የግብርና ግብአቶች ተጠቃሚ ሆነው ለመመረጥ የእርሻ መሬት ያላቸው፣ የአከባቢው ኑዋሪዎች የሆኑ፣ በሬ የሌላቸውና የሚሰጣቸውን በሬና የእርሻ መሣሪያዎች ላለመሸጥ የሚስማሙ መሆን እንዳለባቸው የሚል

መስፈርት ነበር፡፡ ከደርግ መንግስት ለውጥ በኋላም 1984 እስከ 1995 ዓ.ም ከተለያዩ ለጋሾች (ጀርመን አግሮ አክሽን፣ አውሮጳ ህብረት፣ ትሮኬር፣ ሬድ ባርኔት ኖርዌይ፣ አክሽን ኤይድ፣ ከኢትዮጵያ መንግስት፣ ከተመድ ስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽንና ሲኤችኤፍ/ሲዳ ካናዳ) ለመልሶ መቋቋም ፕሮግራም ማስፈፀሚያ ብር 47,441,991 ተገኝቶ ለ 61,911 ገበሬዎች 1,225 በሬዎች፣ የእርሻ መሣሪያዎች፣ የተለያዩ ዘሮችና ማዳበሪያ እንዲሰጣቸው ተደርጓል፡፡

ሌላ ከመልሶ መቋቋም ፕሮግራም ጋር የተያያዘ ስራ የተሰራው በጦርነቱና በድርቁ ምክንያት ከ100 በላይ የሆኑ ወላጅ አልባና አሳዳጊ ያጡ ህፃናት ልጆች በማሰባሰብ ትምህርት እየተማሩ እንዲያድጉ አንገረብ (ታች አርማጭሆ) በተባለ ቦታ መጠለያና መማሪያ ቦታ በማዘጋጀት እንዲረዱ የተደረገበት ፕሮግራም ነው። በህፃናት ማሳደጊያው ህፃናቱን የሚንከባከቡ ሰራተኞችና መምህራን ተመድበው የሚያስተምሩበት ሁኔታ ነበር። በ1977 እና በ1978 ዓ.ም ኢዕማድ ህፃናቱንና ለመርዳት የሚያስችለው በዓየነትና በገንዘብ ድጋፍ ሲያገኝ የነበረው ከአለምአቀፍ ቀይ መስቀል ኮሚቴ (ICRC) ከተባለ ድርጅትና አከባቢውን ሲያስተዳድር ከነበረው የፖለቲካ ድርጅት ኢህዴን ነበር። ከደርግ መንግስት መውደቅ በኋላም ኢዕማድ ለህፃናቱ የሚያደርገው ድጋፍ በመቀጠል በየዓመቱ ትምህርታቸውን ጨርሰው ለስራ ብቁ የሆኑትን ስራ ላይ በመመደብ ወይም ወደ ሌላ ሄደው እንዲሰሩ በመሸኘት በአሁኑ ጊዜ በድርጅቱ ድጋፍ ከሚኖሩት ከሁለት ልጆች በስተቀር ሁሉም እራሳቸውን የሚችሉበት ደረጃ ላይ አድርሶአቸዋል።

### 2.2.3 ከስደት ተመላሾችና ሰፋሪዎች መልሶ መቋቋም ፕሮግራም

በድርቅ፣ በኤኮኖሚና በፖለቲካ ችግር ምክንያት ከረጅም ጊዜ ጀምሮ በርካታ ኢትዮጵያውያን ወደ ሱዳን ተሰደው ይኖሩ እንደነበር በታሪክ የሚታወቅ ነው፡፡ ይህ የመልሶ መቋቋም ፕሮግራም እንዲዘጋጅ ምክንያት የሆነው የደርግ መንግስት ከወደቀ በኋላ በርካታ ስደተኞች ወደ አገር ቤት መመለስ በመፈለጋቸውና በሱዳን መንግስት፣ በኢትዮጵያ መንግስትና በተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽን ስደተኞቹ ወደ አገራቸው በራሳቸው ውሳኔ እንዲመለሱ ስምምነት በማድረጋቸው ነበር፡፡ በዚህ ስምምነት መሠረት ኢዕማድ (አመልድ) የስደት ተመላሾች መልሶ መቋቋም ፕሮግራም በመቅረፅ ከተባበሩት መንግስታት የስደተኞች

ኮሚሽን ጉዳይ (UNHCR) የፕሮጀክት ስምምነት አድርጎ በየዓመቱ ከ15 እስከ 20 ሚልዮን ብር እየተመደበ ከ1985-1993 ዓ.ም ድረስ ስደተኞች እየተቀበለ በተለያየ መንገድ እንዲቋቋሙ አድርጓል፡፡

ከስደት ተመላሾች እንዲቋቋሙ የተደረገው በሁለት መንገድ ነበር፡፡ በአነስተኛ ንግድ ወይም በገቢ ማስገኛ የስራ መስክ ወደ ፈለጉበት አካባቢ በመሄድ መሰማራት ለሚፈልጉት ለእየንዳንዱ የቤተሰብ ሀላፊ ብር 1500 መነሻ ካፒታል፣ የ9 ወር ምግብ፣ 180 ብር የትራንስፖርት አበል፣ ብርድልብስ፣ ለመጠለያ የሚያገለግል ሸራ፣ የምግብ ማበሰያና መመገቢያ ቁሳቁስ በመስጠትና በግብርና የስራ መስክ ለሚሰማሩት ደግሞ እያንዳንዱ ሰፋሪ 1.5 ሄ/ር የእርሻ መሬት፣ በሬ፣ ዘር፣ የመጠለያ ድንኳንና የምግብ ማብሰያ ቁሳቁሶች በማከፋፈል ነበር፡፡ በዚህ መሠረት በአጠቃላይ 43,677 ሰዎች እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡

ከሱዳን ከስደት ተመልሰው ከተቋቋሙት በተጨማሪ በደርግ ጊዜ ከወሎ ክፍለሀገር ተወስደው በጎዴ እርሻ ልማት (የሶማሌ ክልል) ሰፍረው የነበሩ 768 አባወራዎች (1980 የቤተሰብ አባላት) ከአከባቢው ብሄረ ሰብ ጋር በተፈጠረው ቅራኔ ምክንያት ሰፋሪዎቹ በአማራ ክልል በፈለጉት አከባቢ እንዲሰፍሩ መንግስት ሲወስን ኢዕማድ (አመልድ) ሰፋሪዎቹን ለማስፈርና እንደየምርጫቸው ለማጓጓዝ ፕሮግራም እንዲያዘጋጅ በተጠየቀው መሠረት የጎዴ ሰፋሪዎች የመልሶ መቋቋም ፕሮግራም እንዲዘጋጅ ተደረገ፡፡ በእቅዱ መሠረት 416 (975 አባለት ያሉዋቸው) ቤተሰቦች በምርጫቸው መሠረት ወደ ተለያየ አከባቢ የመቋቋሚያ ብር 1500 የምግብና የትራንስፖርት ወጪ እየተሰጣቸው እንዲጓጓዙ ሲደረግ ቀሪዎቹ 352 (988 አባለት ያሉዋቸው) ቤተሰቦች ለእያንዳንደቸው በመተማ የእርሻ መሬት ታርሶ፣ማደበሪያ ተጨምሮና ተዘርቶ፣ የ9 ወር ምግብ ተሰጥቶአቸው እንዲቋቋሙ ተደርጓል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሰፋሪዎቹ በጋራ የሚጠቀሙበት ሁለት ጥልቅ ጉድጓዶች፣ አንድ ወፍጮና የጤና ተቋም ተገንብቶላቸዋል፡፡ ለጠቅላላ ፕሮግራሙ ማስፈፀሚያ በኢትዮጵያ መንግስት የተመደበው ብር 5,508,404 ነበር፡፡

በአጠቃላይ ድርጅቱ ከተመሠረተ ጀምሮ ለመልሶ መቋቋም ፕሮግራም ከተለያሁ ለጋሾች የተገኘው ብር 50,380,940 ሲሆን ለ74,027 ገበሬዎች 8,341 በሬዎች፣ የእርሻ መሣሪያዎች፣ የተለያዩ ዘሮችና ማዳበሪያ በመስጠት እንዲቋቋሙ ተደርጓል።

## 3. የፕሮግራሞቹ ፋይዳ

እላይ እንደተገለፀው የዕለት ደራሽና መልሶ መቋቋም ፕሮግራሞች በመተግበራቸው በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከመሞትና ከመፈናቀል ድነዋል፡፡ በወቅቱ እርዳታ በማግኘታቸው በቀጣይ የምርት ዘመን አምርተው እራሳቸውን መመገብ የቻሉ፣ በሂደትም የተለያዩ የልማት አጋጣሚዎችን መጠቀም የቻሉ አሉ፡፡ ለምሳሌ በ1977 ዓ.ም የድርቁ ሰለባ በመሆናቸው በኢዕማድ የተረዱ በወቅቱም ታጋይ የነበሩ በአሁኑ ጊዜ የሰቆጣ ወረዳ አስተዳደር ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባል የሆኑት አቶ ሰሎሞን መሀመድ (ቡላ) ሁኔታውን ሲገልፁት፡



አቶ ሰሎሞን ሞሀመድ የሰቆጣ ወረዳ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ አባል

"እኔም በ1977 ዓ.ም በድርቁ ከተጠቁና በኢሮ እርዳታ ከተደረገላቸው ሠዎች አንዱ ነበርኩ፡፡ በወቅቱም ደርግ የዋግን ሕዝብ በጠላትነት በመፈረጅ ህዝቡ እርዳታ ለማግኘት ረጅም ርቀት ተጉዞ ደርግ ወደሚቆጣጠራቸው የእርዳታ ጣቢያዎች ቢሄድም ህዝቡ ዕርዳታ እንዲይሰጠው ይደረግ ነበር፡፡ ኢህዴን የሠቆጣ ከተማን ሲለቅና ደርግ ሲገባ አብዛኛው ህዝብ ከኢህዴን ጋር በመውጣት በየገጠሩ ነበር የሠፈረው፡፡ በርካታው የሰቆጣ ከተማ ህዝብ ወደ ደሀና ተሰዶ ነበር፡፡ ህዝቡ ከሰቆጣ ወጥቶ ሲሰደድ በእጁ የያዘው ቀለብም ሆነ ንብረት አልነበረውም፡፡ በወቅቱ የኢሮ

ሠራተኞች የነበሩ እነ አድማሱ ጋጋ ሁለት ጊዜ በደህና፣ ዝቋላ፣ ሰሃላና ላስታ የገንዘብ እርዳታ ሠጥተዋል፡፡ ማርያ የምትባል ከሌሎች ጀርመናዊያን ጋር በመሆን ህክምና ትሰጥ ነበር፡፡ በወቅቱ ከህብረተሰቡ ግልሰቦች እየተመለመሉ በህክምናና በሽታን በመከላከል ላይ ያተኮረ ስልጠና ይሠጥ ነበር፡፡ በዚህም ኢሮ (ERO) ህዝቡን ከበሽታና ከርሃብ በመታደግ ባለውለታው ነበር፡፡ ከእርዳታ በተጨማሪ ለተመረጡ አርሶ አደሮች በሬ፣ የእርሻ መሣሪያዎችና ዘር ይሠጥ ነበር፡፡ ከደርግ ውድቀት በኋላም እርዳታን ከልማት ጋር በማቀናጀት የተፈጥሮ ደኖችን (በኪያ፣ ግባና እና በሰቆጣ አካባቢዎች) በመከለል፣ በውስጡ የተለያዩ ችግኞችን በመትከልና ሠቆጣንና ጀርባ ዮሐንስን የሚያገናኝ የ28 ኪሎ ሜትር የገጠር መንገድ በመስራት ህዝቡ ተጠቃሚ ሆኗል፡፡ በዚሁ መልክ በዋግ ብቻ ሳይሆን በበለሳና በቡግና በቁርጥ ቀን፣ በጨለማ ጊዜ ማንም ባለደረሰበት ፈታኝ ወቅት አመልድ /ኢሮ/ ከህብረተሠቡ ጐን ሆኖ ሁኔታውን ለመለወጥ ከፍተኛ ጥረት ያደረገና በጥረቱም ብዙ የተለወጡ ሠዎች እንዳሉ አውቃለሁ” ብለዋል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው በወቅቱ ድጋፍ ያገኙ ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለህዝብ የሚጠቅም ስራ መስራት የሚችሉበት ደረጃ እንዲደርሱ በር የሚከፍት መሆኑን ነው፡፡

ሌላው በወቅቱ ተጠቃሚ የነበሩ የዝቋላ ወረዳ ፅዝቃ ከተማ ነዋሪ የሆኑት አቶ አዱኛ ታመነ በ1977 ዓ.ም ስለተደረገው ድጋፍና ስለነበረው ሁኔታ ሲገልፁ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

ሙሉ ስም <u>አቶ አዱኛ ታመነ</u> ዕድሜ <u>51</u> ፆታ <u>ወ</u>
የጋብቻ ሁኔታ <u>ባለትዳር</u> ቀበሌ <u>01</u> ጐጥ <u>ቀጠና1</u>
የልጆች ብዛት <u>5</u> ወ <u>2</u> ሴት <u>3</u>
የትምህርት ሁኔታ <u>አራቱ የተማሩ</u>
የባለቤቱ/የአባወራ/ ስም <u>ዘነበች ግብር</u> ዕድሜ <u>44</u>



“እኔ በዕድሜዬ 3 መንግስታትን አሳልፌአለሁ፡፡ በተለይ በዋግ ዝቋላ ወረዳ ከ1975 - 1976 ዓ.ም ጀምሮ ከፍተኛ ድርቅ በመከሰቱና በደርግና በኢህዴን መካከል በተደረገው ጦርነት ምክንያት የዕለት ጉርስ በማጣቱና እርሻ ለማረስ የሚያስቻል ሰላማዊ ሁኔታ ባለመኖሩ አርሶ አደሩ ለስደትና ዕንግልት ተጋልጧል፡፡ በዚያን ወቅት ጉልበት ያለው ኢህዲንን በመወገን ወደ ትግሉ ሲገባ መታገል የማይፈልገው ወደ ሱዳንና ኮረም ለመሄድ ሲገደድ ጉልበት የሌላቸው ሽማግሌዎች፣ አቅም የሌላቸው ህፃናትና ሴቶች ደግሞ ቦታቸውን ሳይለቁ የመጣውን የረሃብ አደጋ ለመቀበል ተገደው ሲጠብቁ በ1977 ኢሮ ኢዕማድ/በኢህዲን ነፃ መሬት በዝቋላ ወረዳ ቀበሌዎች ከውጭ ድርጅቶች ጋር በመተባበር የእህል መግዣ ገንዘብ ለአንድ ሰው 7 እና 8 ብር እንደ ቤተሰቡ ብዛት በመስጠቱና ተረጂው ደግሞ ከደጋው፣ ከጎንደር፣ ከዕብናትና ኮረም በመሸመት እራሱን ለማትረፍ ችሏል፡፡ ረሃቡ ባደረሰው ችግር ምክንያት ከፍተኛ የኮሌራ በሽታ ገብቶ ነበር፡፡ በሽታውን ለመቋቋም ከዕርዳታው በተጨማሪ ኢሮ የህክምና ዕርዳታ  አድርጓል፡፡ ኢሮ በሚሰጠው ብር እህል ለመግዛት ተጠቃሚዎችና ነጋዴዎች ወደ ኮረም፣ ደባርቅና ጃናሞራ ሲሄዱ ደርግ በማፈስ ወደ ሠፈራና ብሄራዊ ውትድርና ይወስዳቸው ስለነበር ነጋዴው እህል ገዝቶ ለማቅረብ ይቸገር ነበር፡፡ ሆኖም ግን በ1978 ዓ.ም ዝናብ በመዝነቡ ኢሮ ከሰጠው ብር ቆጥቦ ዘር ገዝቶ በመዝራቱ በቂ ምርት እንዲያመርትና ለቀጣዩ የ1979 ዓ.ም ለዘር የሚያገልግል እህል እንዲኖረን የኢሮ እርዳታ ረድቶናል፡፡ ከስደት የተመለሰውንና በድርቅ የተጎዳውን ሰው ለማቋቋም የበሬ፣ የእርሻ መሳሪያና ዘር ገዝቶ በመስጠት ለማቋቋም ተችሏል፡፡ በ1977 ዓ.ም በደርግ ቁጥጥር ስር በነበሩት የኮረም፣ የሰቆጣና የዕብናት ከተሞች በገባው የኮሌራ በሽታ ምክንያት በሺ የሚቆጠር ሰው ሲሞት በዝቋላ ወረዳ ግን ሳይታወቁ ከሞቱት ውጭ ኢሮና የኢህዴን ሀኪሞች ባደረጉት ርብርብ ማንም ሰው ሳይሞት ማትረፍ በመቻሉ ህዝቡ ከእርሻውና ከዕለትተለት ስራው ሳይደናቀፍ እንዲንቀሳቀስ ለማድረግ ተችሏል” ብለዋል፡፡በተጨማሪ ኢሮ እራሳችንን እንድንችል በ1986 ዓ.ም የእርሻ በሬ፣ የበሬ ዕቃና ዘር በ1147 ብር ገዝቶ ስለሰጠኝ፣ በየዓመቱ የተሻለ ምርት እንዳገኝ በማስቻሉ፣ 4 ክፍል ቆርቆሮ ቤት ሰርቻሁ ቴሌቪዥንም ገዝቻለሁ ከብቶችም አሉኝ ልጆች እያስተማረኩ አንዱን ትምህርት አስጨርሸ ስራ እስከማስያዝ አድርሻለሁ ኑሮዬ ተሻሽሏል” ብለዋል፡፡

አቶ አለማየሁ አዳነ በ77ቱ ድርቅ ህዝባዊ ሀኪም የነበሩ በአሁኑ ጊዜ በዝቋላ ወረዳ በአቅም ግንባታ ፅ/ቤት የሚሰሩ የረሀብንና በሽታን ችግር በመፍታት ምን ያህል ኢ.ዕማድ ውጤታማ እንደነበር የሚከተለውን ብለዋል፡፡



ሙሉ ስም <u>አቶ አለማየሁ አዳነ</u> ዕድሜ <u>43</u> ፆታ <u>ወ</u>
የጋብቻ ሁኔታ <u>ባለትዳር</u> ቀበሌ <u>01</u> ጐጥ <u>ሰቆጣ</u>
የልጆች ብዛት <u>6</u> ወ <u>5</u> ሴት <u>1</u>
የትምህርት ሁኔታ <u>ሁሉም በትምህርት ላይ</u>
የባለቤቱ/የአባወራ/ ስም <u>ብናይሽ ሚሊዮን</u> ዕድሜ <u>32</u>

"ወቅቱ የኮሌራ በሽታ የተከሰተበት ነበር። በቦታው ወጣ ገባነትና የተራራቀ መሆን መድሃኒት ለማቅረብና ህክምና ለመስጠት አስቸጋሪ የነበረ ቢሆንም ኢ.ሮና ኢ.ህዴን የቤት ለቤት ህክምና በመስጠት ከፍተኛ ስራ ሰርተዋል፡፡ ችግሩን ለማቃለል ትንሽ ትምህርት ያላቸውን የአካባቢ ሰዎች በማሰልጠን የቤት ለቤት ህክምና አገልግልሎት እንዲስፋፋ ተደረገ፡፡ በሌላ በኩልም መለስተኛ ሆስፒታል መሽሀ ተከዜ ላይ አቋቁሞ ኢ.ሮ ህክምና ይሰጥ ነበር፡፡ ርሃቡን ለማቃለል ኢ.ሮ እህል የሚያቀርቡ ነጋዴዎችን በማደራጀትና የመነገጃ ብር በብድር በመስጠት እህል ካለበት ገዝተው እንዲያቀርቡና ተረጂው በተሰጠው ብር ከነጋዴዎቹ እህሉን ገዝቶ እንዲጠቀም በማድረግ ችግሩን መቋቋም ተችሏል፡፡ ከኢ.ሮ ጋር ከጀርመን የመጣ የህክምና ቡድን ነበር። በዚህም ወቅት ኢ.ሮ ባይኖር ህዝቡ በበሽታ ያልቅ ነበር፡፡"



**<u>ቄስ መላሹ ፀጋዬ</u>**

ሙሉ ስም <u>ቄስ መላሽ ፀጋዬ</u> ዕድሜ <u>51</u> ፆታ <u>ወ</u>
የጋብቻ ሁኔታ <u>ባለትዳር</u> ቀበሌ <u>01</u> ጐጥ <u>ሰቆጣ</u>
የልጆች ብዛት <u>6</u> ወ <u>3</u> ሴት <u>3</u>
የትምህርት ሁኔታ ሁለቱ ያጠናቀቁ ሌሎች በመማ
የባለቤቱ/የአባወራ/ ስም <u>ሙሉ ይማም</u> ዕድሜ <u>47</u>

ቄስ መላሹ ፀጋዬ በድርቁ ጊዜ በመልሶ መቋቋም ፕሮግራም የበሬ ተጠቃሚ የነበሩ በኋላም የኢዕማድ የእርዳታና መልሶ መቋቋም ኮሚቴ አባል የነበሩ በተሰጠው ድጋፍ ምክንያት በተጠቃሚዎች ህይወት ላይ የመጣውን ለውጥ የሚከተለውን ብለዋል፡፡

"ቀደም ሲል ኢ.ሮ እየተባለ ይጠራ የነበረው ድርጅት ባካባቢያችን በነበረው ጦርነትና ድርቅ ምክንያት ሲንገላታና ወደ ኮረምና ጎንደር ሲሰደድ የነበረን ህዝብ በችግሩ ደርሶለት የዕለት ዕርዳታ በመስጠት ህዝቡን ለመታደግ በቅቷል፡፡ ከዕርዳታው በተጨማሪ ኢ.ሮ አለ ሲባል ከጎናችን የቆመ ድርጅት አለ በሚል ከተስፋ መቁረጥ ወጥቶ በአካባቢው ተረጋግቶ እንዲቀመጥ ሞራል ሰጥቶታል፡፡ ነጋዴው በማደራጀት እህል ካለበት ቦታ ገዝተው አምጥተው ለህዝቡ እንዲሸጡ አድርጓል፡፡ በኋላም ከዕለት ዕርዳታው ውጭ በመልሶ መቋቋም ፕሮግራም በሰቆጣ ዙሪያ ወረዳ በነበሩት ቀበሌዎች ቢያንስ በቀን በ50 በሬ በላይ እየተገዛ በተከታታይ በሬ ለሌላቸው አ/አደሮች በማደል የእርሻ መሳሪያ ማለትም ማረሻ ወገል ማጭድ፣ ዘር የመሳሰሉትን በመስጠት ወደ መደበኛ የምርት ስራ እንዲገቡ ተደርጎ ጥሩ ምርት በማምረት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል፡፡

እኔም በወቅቱ በሰቆጣ ወረዳ አንድነት ቀበሌ የእርዳታና የመልሶ መቋቋም ኮሚቴ ሆኜ ተረጂዎችን በመለየትና በመመልመል ከኢ.ሮ ጓዶች ጋር በመሆን የዕለት ዕርዳታ ማለትም ስንዴ፣ ዘይት፣ ባቄላ፣ ምስር እናከፋፍል ነበር፡፡ ህዝቡ ከዕርዳታ ጣቢያ ቦታ ሳይንገላታ የተቀበለውን እህል ሳይሸጥና ችግር ላይ ሳይወድቅ ሠራተኞቹ ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በወቅቱ በመሸኘት የተቀበለውን የዕርዳታ እህል ይዞ ወደ ቤቱ በወቅቱ እንዲሸኝ ያደርጉ ነበር፡፡ ህዝቡም በሚደረግለት እንክብካቤ ደስተኛ ሆኖ ነበር ያለምንም መጉላላት የዕርዳታ ስርጭቱን ያከናውን ነበር፡፡

በዚያን ወቅት አንደ በሬ የሰጠናቸው ሰዎች ዛሬ ባለጥንድ በሬ፣ ላም፣ ፍየል፣ በግ ባለቤት ሆነው ተሸላሚ እስከመሆን ደርሰዋል፡፡

በአጠቃላይ ድርጅቱ በድርቁ ወቅት ህዝቡ ድጋፍ ባያገኝ እንደተሰደደ ይቀር ነበር። ምክንያቱም በሬና ዘር መግዣ አልነበረውም፡፡ በአንድ ወቅት በተፈጠረ ችግር የዘላለም ጠባሳ ይዞ ይቀር ነበር፡፡ አመልድ በወቅቱ በመድረሱ ግን አሁን ለአለበት ደረጃ በቅቷል፡፡ እኔም በወቅቱ በሬ ተሰጥቶኝ በመቋቋሜ በከተማ ቤት ሠርቼ ልጆቼንም እያስተማርኩ እገኛለሁ፡፡ መሠረቴ ይኸው ድርጅት ነው፡፡ በወቅቱ

የተረዱና በሬ የተሰጡ ሌሎች ግለሰቦችም አሉ፡፡ ለምሳሌ እሸቱ ገብሬ በጣም ድሀ ነበር። አሁን አሉ ከሚባሉ ጠንካራ አርሶ አደሮች የሚመደብ ነው፡፡ በሰቆጣ ከተማ ቤት ሠርቶ ልጆቹን እያስተማረ ነው ቤትም እያከራየ የተሻለ ኑሮ ይኖራል” ብለዋል፡፡



ከስደት ተመላሽ የሆኑ <u>አለቃ ገብረስላሴ ገ/ሚካኤል</u> ስለሁኔታውና ድጋፉ ስላስገኘላቸው ፕሮግራም ሲገልፁ “እኔ ደርግ ወደ ስልጣንና አካባቢው ከመምጣቱ ከ1962 ዓ.ም ጀምሮ የአካባቢው ኗሪ ነኝ፡፡

በአካባቢው ከፍተኛ ዝርፊያና ተኩስ ስለነበር በአካባቢው በሰላም መኖር አልተቻለም ነበር፡፡ በ1969 ዓ.ም ደግሞ የአካባቢውን ህዝብ በግዳጅ ወደ አርማጭሆ ካልዘመታችሁ ብሎ ስለአስገደደን አካባቢውን ጥለን ወደ ሱዳን ለመሰደድ በቃን፡፡ ሶፋዋ በሚባል የሱዳን የስደተኞች ካምፕ ስንኖርም በየጊዜው በተለያዩ ምክንያት በሱዳን ወታደሮች ድብደባና እንግልት ይደርስብን ነበር፡፡ የደርግ መንግስት ከወደቀ በኋላ በ1986 ዓ.ም ወደ አገራችን እንድንገባ ጥሪ ሲተላለፍ እኛ ሁመራ እንስፈር ብለን ብንጠየቅም ወደ ትውልድ አገራችሁ ካልሆነ በስተቀር ሁመራ አናሰፍራችሁም በመባላችን እኛ ደግሞ ብዙ ቤተሰብ ይዘን ወደ ትውልድ አገራችን ብንሄድ ጠባብ መሬት ላይ መቋቋም ስለማንችል ወደ ትውልድ ቦታችን አንሄድም ብለን እስኪወሰን ድረስ ኰኪት መተማ ቆይተናል፡፡ በኋላ ከተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ኮሚሽን (UNHCR) ጋር በተደረገው ስምምነት መሰረት ወደ አብድራፊ እንድንገባ ከተደረገ በኋላ መቋቋሚያ ይሰጠን ብለን በጠየቅነው መሰረት ለአንድ ቤተሰብ 1500 /አንድ ሺህ
አምስት መቶ ብር/ እና የ9 ወር ቀለብ እንደሁም የቤት ቁሳቁስ ተሰጥቶናል፡፡ በዚህም እኔ ከተረጂነት ወጥቻለሁ፡፡ ቤት ሰርቻለሁ ከ50-70 ኩንታል (ወደ 70000 ብር የሚገመት) ሰሊጥ በየዓመቱ አመርታለሁ” ብለዋል፡፡



ሙሉ ስም አቶ ወንድሙ ታደሠ ዕድሜ 39 ፆታ ወ
የጋብቻ ሁኔታ ባለትዳር ቀበሌ ኰኪት ጐጥ ጐዴ
የልጆች ብዛት 5 ወ 4 ሴት 1
የትምህርት ሁኔታ ሦስቱ በትምህርት ላይ ያሉ
የባለቤቱ/የአባወራ/ ስም ወ/ሮ ዳሳሽ ፋንታው ዕድሜ 28

ሌላው ከስደት ተመላሽ አቶ ወንድሙ ታደሠ ስለሁኔታው ፕሮገራሙ ያስገኛላቸውን ጥቅም ሲገልፁ "የተሰደድኩት በ1977 ዓ.ም ከወሎ ከዋግ ኽምራ ወደ ሱዳን ነበር የተሰደድኩበት ምክንያት በወቅቱ በነበረው የፖለቲካ ችግርና አካባቢው ድርቅ ስለነበረ ነው፡፡ እስከ 1985 ዓ.ም ድረስ ሱዳን ውስጥ በቀይ መስቀል ድጋፍ በስደተኞች ካምፕ ስኖር ነበር፡፡ ከቀይ መስቀል ድጋፍና ዕርዳታ በተጨማሪ በግሌም እስራ ነበር፡፡ በ1985 ዓ.ም ወደ አገር ቤት እንድንገባ ጥሪ ሲቀርብ በፍላጐቴ በመመዝገብ ወደ መተማ/ጎንደር/ ስንገባ የተቀበለን የአሁኑ አመልድ የቀድሞው ኢ.ሮ ነበር፡፡ በወቅቱ የተመዘገብኩት በንግድ ሥራ ለመሰማራት ስለበር ለመቋቋሚያ ብር 1500 /አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/፣ የ9 ወር ቀለብ፣ የቤት ውስጥ ቁሳቁስ የተለያዩ ብስኩቶችና የመጠለያ ሸራ ተሰጥቶኛል፡፡ በኋላ ግን የንግድ ሥራው ብዙ አላዋጣኝ ሲል የእርሻ መሬት ተቀብዬ በማረስ የተለያዩ ምርቶችን ማምረት ችያለሁ፡፡ በዓመት ምንም እንኳን መጠኑ የተለያየ ቢሆንም እስከ 15 ኩ/ል ማሽላ፣ ጥጥና ሰሊጥም አምርቻለሁ፡፡ ከእርሻ ውጤት ባገኘሁት ምርትና ገቢም አንድ ጋሪ/ካሮ/ና 6 ላሞች ገዝቻለሁ፡፡ አንድ ቆርቆሮ ቤት ሰርቻለሁ፣ 7 ቤተሠቦቼን ለማስተዳደርና 3 ልጆቼን ለማስተማር በቅቻለሁ፡፡ ከስድት የተመለሱ ሌሎች በኢ.ሮ የተቋቃሙ ጓደኞቼም ሀብታም ሆነዋል፡፡ ለምሳሌ፡- አቶ ግርማይ አበበ መጀመሪያ ከስደት ሲመለስ ምንም አልነበረውም። በአሁኑ ሰዓት ግን ከኢ.ሮ ባገኘው መቋቋሚያ ተነስቶ 20 ከብቶችና የመኖሪያ ቤት አለው፡፡ እንደዚሁም ሌላው አቶ ካሳዬ አማረ የተባሉ ጓደኛዬ ደግሞ ኢ.ሮ በሠጠው መቋቋሚያ ሱቅ ከፍቶ አነሰ ቢባል ወደ ብር 180,000 ግምት ያለው ንብረት ማፍራት ችሏል፡፡

ሌላዋ ደግሞ ስንዱ የምትባል ወደ 38 ከብቶች አሏት፣ ራሷን ማስተዳደር ችላለች፡፡ ሌላው ጋሻው የተባለ ከስደት ሲመለስ ገና ልጅ የነበረ በአሁኑ ጊዜ ሱቅ ከፍቶ እስከ 80,000 ካፒታል እያንቀሳቀሰ፣ ቤትም ሠርቶ ቤተሠቡን በጥሩ ሁኔታ በመምራት ላይ ይገኛል። ሌላ አቶ አበራ በቀለ ከኛ ጋር ኮኪት የሰፈሩ የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ፣ ከስደት ከተመለሱ በኋላ ኢ.ሮ በሰጣቸው መቋቋሚያ መነሻ በማድረግ በአሁኑ ሰዓት 200,000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር / የሚገመት መኖሪያ ቤት ጐንደር ላይ ገዝተው መኖሪያቸውን ጐንደር ከተማ በማድረግ ደለሎ ላይ 100 ሄ/ር መሬት ወስደው በኢንቨስተርነት ሲሰሩ ይገኛሉ ” ብለዋል፡፡



ሙሉ ስም አቶ ጋሻው ግዛው ዕድሜ 33 ፆታ ወ
የጋብቻ ሁኔታ ባለትዳር ቀበሌ ኮኪት ጐጥ ቀጠና 7
የልጆች ብዛት 3 ወ --- ሴት 3
የትምህርት ሁኔታ ሁለቱም የተማሩ
የባለቤቱ/የአባወራ/ ስም ወ/ሮ ፀሐይ ሞላ ዕድሜ 28

አቶ ጋሻው ግዛው የተባሉ ከሱደን ስደት ተመላሹ አሁን ኮኪት ኗሪ የሆኑ ስለሁኔታው አሁን ሰላሉበት ሁኔታ ሲገልፁ “ከስደት ስመለስ ገና ልጅና ወንደላጤ ስለነበርኩ በወቅቱ ለሁለት ወንደላጤ አንድ በሬ፣ ለባልና ሚስት ደግሞ አንድ በሬ ይሰጥ ነበር፡፡ በዕደላው ወቅት እኔ በቦታው ስላልተገኘሁ ከሌላ ግለሰብ ጋር ተጣምሬ በሬ ሳይሰጠኝ የታለፍኩ ቢሆንም ተመልሸ ብቻዬን ስቀርብ በግማሽ የበሬ በጀት አንድ ወይፈን ተገዝቶ ተስጥቶኝ በወቅቱ ልጅ ስለነበርኩ በአቅሜ የጉልበት ሥራ እየሠራሁ ወይፈኑ ለእርሻ እስኪደርስ ከጠበኩ በኋላ የአካባቢው ሠዎች ከበሬ ይልቅ ላም ይሻልሃል ብለው ስለመከሩኝ በሬውን በ800 ብር ለሌሎች ከስደት ተመላሾች ሽጬ ላም ገዝቼ ላሚም እየወለደች ከብት ማርባት ቻልኩ፡፡ በአሁኑ ሰዓት 4 ላሞች፣ 3 ጥጆች አሉኝ። አሁን መሬቱ ቢያረጅም ለጊዜው የተሰጠኝን የእርሻ መሬት እያረስኩ ምርት ማግኘት ችያለሁ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የተሰጠኝን ያረጄ መሬት ትቼ ሌላ መሬት በመከራየት ጥሩ ምርት በማምረት ላይ እገኛለሁ፡፡ ኢ.ሮ በሰጠኝ መነሻ ቆርቆሮ ቤት ሠርቻለሁ፣ ቤተሰብ መስርቼ /ሚስት አግብቼ/ 3 ልጆች ወልደናል፡፡ ኢ.ሮማ /ERO/ መወሳት ያለበት ድርጅት ነው፡፡ እየሠፈረ የሠጠን

ስንዴም በረከት አለው፡፡ በተፈጥሮ ችግርና በመንግስት ድጋፍ እጥረት እድገታችን ፈጣን ባይሆንም ኢሮማ የሚረሳ ድርጅት አይደለም፡፡ በአጠቃላይ በአሁኑ ሰዓት እራሴን ችያለሁ” ብለዋል፡፡



ሌላው ከስደት ተመላሽ አቶ አሰፋ ገ/የሱስ በአሁኑ ጊዜ የ02 አብደራፊ ቀበሌ አስተዳዳሪ ስለሁኔታው ሲገልፁ “በርካታ ህዝብ በፊት የነበሩ ገዢ መደቦች ባደረሱበት ጭቆናና የቀይ ሽብር ዘመቻ ምክንያት በየጊዜው ወደ ሱዳን እንዲሰደድ ተደርጓል፡፡

እኔ ራሴም ደርግ ሊያስረኝ ይከታተለኝ ስለነበር ከሱዳን ስደተኞች መካከል አንዱ እንድሆን ተገድጄ ነበር፡፡ በ1983 ዓ.ም ደርግ ሲወድቅ በርካታ ስደተኞች ከሱዳን ወደ አገር ቤት ተመልሰዋል፡፡ ከስደት ተመላሾች ምዝገባ ሲካሄድና ሁሉም ወደ የትውልድ ቦታው ነው የሚመለሰው ሲባል እኛ አልተቀበልነውም፡፡ ምክንያቱም ወደ ሱዳን ስንሰደድ ቤተሰብ አልመሠረትንም ነበር፡፡ ከስደት ስንመለስ ግን ልጅ ወልደን ቤተሰብ መስርተን ስለነበርና የትውልድ አካባቢያችን መሬት ደግሞ ተከፋፍሎ ያለቀ ስለነበር ብንሄድ የምናገኘው ነገር ስለሌለ አልተቀበልነውም፡፡ በወቅቱ ወደ አገር ቤት ለመመለስ መግቢያ በር የነበረው ኢሮ በሚሰራበት የአማራ ክልል መተማ ስለነበር በመተማ በኩል ገበተን ምርጫችን አብደራፊ ስለነበር ወደ አብደራፌ ከሄድን በኋላ በቤተሰብ 1500 /አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር/ የ9 ወር ቀለብ የቤተሰብ ቁሳቁስ /ማንኪያ፣ ብረት ድስት/ ባልዲና ጀሪካንና የመሣሰሉትና ለመጠለያ የሚያለግል ሸራ ተቀብለናል፡፡ በአሁኑ ጊዜ በተደረገልኝ የመልሶ ማቋቋም ድጋፍ ተነስቼ 3 ክፍል ቤት ሰርቻለሁ እስከ 60 የሚደርሱ በግና ፍየል/ 3 አህዮች አሉኝ ጋሪም አለኝ በተሰጠኝ የእርሻ መሬት ላይ በዓመት ከወጪ ቀሪ እስከ 20,000 ብር ገቢ አገኛለሁ፡፡ በዚህም ራሴን ችያለሁ ልጆቼን እያስተማርኩ ነው ዩኒቨርስቲም የደረሰ ልጅ አለኝ” ብለዋል፡፡

## 4. የዕለት ደራሽና መልሶ መቋቋም ፕሮግራሞች ለምን ስኬታማ ሆኑ?

1. የህዝብን ችግር መፍታት አላማዬ ብሎ የተነሳና በውጤቱም ተጠቃሚ እንሆናለን በሚል በቁረጠኝነትና በታማኝነት የሚሰራ ሰራተኛና ባለሙያ በድርጅቱ በመኖሩ፣
2. ከዓላማው የሚመነጭ ጠንካራ የስራ ባህል በድርጅቱ እያደገ መምጣቱ፣
3. በእቅዶች ዝግጅትና አፈፃፀም የህዝብ፣ የአስተዳደር ወይም የመንግስት አካላትና ተሳትፎ የነበረ መሆኑና አመልድ ከነዚህ አካላት ጋር ተቀናጅቶ መስራቱ ፣
4. በወቅቱ የተሻለ ልምድ ከነበራቸው አገር በቀልና የውጪ መንገስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በተለይ ከማህበረ ረድኤት ትግራይ (ማረት) ጠቃሚ ልምድ መቅሰም መቻሉ ዋና ዋናዎቹ ነበሩ።